# ፍ ት ሻ - ል ብ ወ ለ ድ
# ክ ፍ ል  አ ን ድ

*ከሥርጉተ ሥላሴ*
*ነሐሴ 2000 ዓ. ም.*

**ተረት - ተረት ...ልጆች**
**የላም - በረት ... አላችሁ ልጆች ?...**

ፍትሻ የምትባል አንዲት ጠይም ትንሽዬ ልጅ ነበረች። ፍትሻ ዕድሜዋ ዘጠኝ ነው። የፍትሻ ወላጆች ሌላ ልጅ አልነበራቸውም። አንድ*ያ* ልጃቸው ፍትሻ ናት። ስለሆነም ፍትሻ የምትፈልገውን ነገር ወላጆቿ ያደርጉላታል። እሷም ወላጆቿ አደርጊ የሚሏትን፣ የሚፈቅዱላትን ብቻ ታደርጋለች። አታድርጊ አይጠቅምሽም ጥሩ አይደለም የሚሏትን ደግሞ አታደርግም። ፍትሻ የወላጆቿን ምክር የምትቀበለው ጎበዝ ልጅ ናት።

አንድ ቀን አባትና እናቷ እሷን ሳይዙ ገብያ ይሄዱና ለልደቷ የሚሆን ቆንጅዬ ልብስና ጫማ ገዙላት። ፍትሻ ከትምህርት ቤት ስትመለስ ቀኑ የተወለደችበት ዕለት ስለነበረ የሰፈሩን ልጆች፣ አብረዋት ያደጉትን ሁሉ አሰባስበው ፋንታ፣ ሚርንዳ፣ ኮላ፣ ብስኩት፣ ከረሜላ፣ ድፎ ዳቦ፣ ኬክ፣ ሻሂ፣ አዘጋጅተው ነበር የጠበቋት። ፍትሻ ቤት ስትገባ ሁሉ ነገር ተሟልቶ ጠበቃት። ፍትሻ ከት ከት ብላ ሥቃ ደስታዋን ለእንግዶቿና ለወላጆቻ ገለጠችላቸው። ከዛ... ሮጣ ሂዳ የገዙላትን ስጦታ በፍጥነት ከፍታ ስታየው የልብሱም የጫማውም ቀለም ነጭ ነበር።...

ከዛ ፍትሻ ምርር ብላ አለቀሰች። የስጦታው ቀለም በፍፁም ደስ አላላትም ነበር። ለምን መሰላችሁ ልጆች ፍትሻ ያለቀሰችው? የተገዛላት ስጦታ ቀለሙን አልወደደቻውም ነበር። ምክንያቱም እሷ የምትወዳቸው ቀለማት አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ናቸው። ፍትሻ እነኝህን ቀለማት የምትወዳቸው ቀለማቱ የሀገራችን የኢትዮጵያ ባንዲራ በመሆናቸው ነው። ከዛ በኋላ ባቢና ማሚ ስታለቅስባቸው በጣም ደነገጡ። ፍትሻንም አቆላመጧት እንዲሁም አባበሏት። ሲነጋ በጥዋቱ ሄደው የምትፈልገውን ዓይነት ቀለም ያለበትን ልብስና ጫማ እንደሚገዙላት ቃል ገቡላት። ... ከዛ ፍትሻ ደስ ብሏት የልደት በዓሏ ሥርዓት በፍሰሐ ተከናወነ።

**ልጆች ክፍል 2 ፍትሻ ይቀጥላል ...**